# <u>ሉዓላዊነታችን ይከበር!</u>

ከባህልቢ ዘማርያም

ይህ ፀሓፊ ረዘም ላለ ጊዜ ከተሳትፎ ውጭ የነበረ ቢሆንም፣ ይኸው ዛሬ “ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና “ሉዓላዊነታችን ይከበር” በሚል ርእስ የአቅሙን ለማካፈል ብቅ ብሏል።

እውነቱን ለመናገር ይህ ፅሑፍ በርካታ የተዋጣላቸው ኢትዮጵያዊ ወገኖች በተለያየ መልኩ የከተቧቸውን ሓሳቦች ለማጠናከር የተዘጋጀ እንጂ የተለየ መፍትሔ ይዞ የቀረበ አለመሆኑ አንባቢ ከወዲሁ ቢረዳው መልካም ነው። ሆኖም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች በጥልቀት ያቀረቡዋቸውን ሓሳቦች ማጠናከር በራሱ ለሥራዎቻቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እውቅና መስጠትና መደገፍን ስለሚያመላክት ይህ ፀሓፊ ለነዚህ በርካታ ወገኖች ያለውን አክብሮት፤ አድናቆትና ወገናዊነትን ያረጋግጣል። በመሆኑም በተያዘው ርእስ ላይ ሃተታውን ያሰፍራል።

ይህ ሉዓላዊነታችን ይከበር የሚለው ርእስ የተመረጠበት ዋና ምክንያት ያገራችን ዳር ድንበርን አስመልክቶ የቀደመው የኢትዮ-ኤርትራ “የድንበር ግጭት” ተገቢ መቋጫ ሳያገኝ በእንጥልጥል የሚገኝ ከመሆኑም በላይ መጨረሻ ላይ ሊደረስበት የሚችል ውጤትም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ኣሳልፎ የሚሰጥ እንዳይሆን ስለሚያሰጋ ነው።  ይህ ብቻም ሳይሆን፤ ዛሬ ኢህአዴግ ከሱዳን መንግሥት ጋርም ሌላ የድንበር ማካለል ድርድር እያካሄደ መሆኑ በስፋት እየተነገረ መገኘቱ ሌላ አሳሳቢ ጉዳይ ይሆናል። ይህ ፀሓፊ ለጊዜው ከሱዳን ጋር እየተካሄደ ነው ስለሚባለው የድንበር ማካለል ድርድር ላይ ሰፋ ያለ አስተያየት ለማቅረብ የሚያስችል በቂ መረጃ የሌለው በመሆኑ ለጊዜው ትችት ከማቅረብ ይቆጠባል። ሆኖም ካለፈው ስሕተት መማር ብልህነት ነውና ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትና ከተገኘው ውጤት ትምህርት መወሰድ አለብን ብሎ ያምናል። ኤርትራ “በድንበር ይገባኛል” ጥያቄ ሰበብ በከፈተችብን ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ እልቂት፣ የሰላማዊ ህዝብ መፈናቀልና የንብረት ውድመት ደርሷል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን መሰል አጥፊ የእብሪት ጦርነት መመከት ነበረበትና በተባበረ ክንዳቸው መከቱት። እብሪተኛውን በመረጠው መንገድ ገጥመው አሸነፉት። አሸነፉት ብቻም ሳይሆን ለመከላከያነት በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ቀበሩት። ለሁለት ዓመት ተለምኖ ከሉዓላዊ ግዛቶቻችን አልውጣም በማለት ህዝባችንን እያሰቃየና መሠረተ-ልማቶቻችንን እያፈራረሰ ከቆየ በኋላ ከኢትዮጵያ ህዝብ አይበገሬ ክንድ እንዲያስጥሉት የተባበሩት መንግሥታትን ተማጸነ። ከአራት ኪሎ ቤተ-መንግሥትም ትብብር ተሻረውና ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ ባልሆነ መንገድ አሸናፊው ጦር ጠላትን የማሳደዱ ተግባር እንዲያቆም ትእዛዝ ተሰጠው፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይም በዛው እንዲያከትምለት ተደረገ። የሕግ መሠረት የሌለው የአልጀርሱን ውል በመፈረምም ኤርትራ አላገባብ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛቶች ባለቤት እንዲትሆን ተደርጓል። ከዚህ በመነሳት ይህ ፀሓፊ አገዛዙ ለሉዓላዊነታችን ያለው ቀናኢነት አስተማማኝ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጦርነት በገንዘብ ሊተመን የማይችል መስዋእትነት የተከፈለበት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። አሌ የማይባል ሕይወትና ንብረት ተከፍሎበታል። ሆኖም የተመዘገበው ውጤት ለሉዓላዊነቱ ቀናኢ የሆነ መንግሥት እንደሌለን በግልጽ ያሳየ አሳፋሪም አስነዋሪም ነው። ይህንን አሳፋሪ ውጤት ለተገነዘበ ሁሉ ከሱዳን ጋር እየተደረገ ያለው የድንበር ማካለል ድርድር ውጤት በባሰ መልኩ አሳፋሪ ሊሆን እንደሚችል የሚጠበቅ ነው። የኢትዮ ሱዳን የድንበር ኮሚቴ እያወጣቸው ያሉ መግለጫዎችም የሚጠቁሙት ይህንን ሃቅ ነው። በመሆኑም ከኢትዮ-ሱዳን የድንበር ማካለል ድርድር የምንጠብቀው ካለፈው የተለየ ይሆናል ብሎ መጠበቅ የሚቻል አይሆንም። ኢትዮጵያዊ ዳግም ሓፊረት እንዳይከናነብና “ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ” እንዳይሆን ከወዲሁ ነገሮችን በአንክሮ መመልከትና እየተካሄደነው የሚባልለት ድርድር ለህዝብ ውይይት እንዲቀርብ ገዥዎቻችንን ማስገደድ ይጠበቅበታል። ይህንን የማስገደድ አቅም ግን በተናጠል ጉዞ ለማሳካት እንደማይቻል ያለፉት ተሞክሮዎቻችን በግልጽ ያሳዩን ስለሆነ ቢያንስ በአገር ጉዳይ ላይ በጋራ የመቆም አስፈላጊነትና ግዳጅ ከወዲሁ ሊሰመርበት ይገባል። የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን በኢትዮ- ሱዳን የድንበር ኮሚሽን አለመተካት የተለየ ውጤት ያመጣል ብሎ መጠበቅ ቢያንስ የዋህነት ይሆናል። ያን ሁሉ መስዋእትነት በመክፈል አውደ ውጊያ ላይ በደም የተመዘገበው ብሔራዊ ድል “በገዢዎቻችን” ፈቃድ የሞቱና የተቀበሩ ሰነዶችን የማካለያ አካል እንዲሆኑ መደረጉ መረሳት የሌለበት ጉዳይ ይሆናል። በመሆኑም፣ ከኢትዮ-ሱዳን የድንበር ድርድር የተለየ ውጤት መጠበቅ አይቻልም። ያን ሁሉ መስዋእትነት የተከፈለበት ሉዓላዊ ግዛት በፈቃዳቸው አስረክበው ያለ አንዳች ሓፍረት በፍርድ ሂደትም አሸንፈናል፤ ሆ በሉ ያሉን “ገዢዎቻችን” ዛሬም በባዶ ሜዳ ሆ እያላቹህ አመስግኑን ማለታቸው አይቀሬ ነው። ከዚህ በፊት አቶ መለስ ለፓርላማ ማብራሪያ ሲሰጡ “አንድም ዜጋ የተፈናቀለ የለም” አሉን እንጂ አንድም መሬት ለሱዳን የተሰጠ የለም ሲሉ አላደመጥንም። ይህ አባባል ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን አለመነጠቃችን አያመላክትም። ያ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለበት የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ሉዓላዊነታችንን በሚያስከብር መልኩ ለመቋጨት ፍላጎት ያላሳዩ “ገዢዎች” በሰላማዊ ድርድር ሉዓላዊነታችንን ሳይሸራረፍ ያስከብራሉ ብሎ መጠበቅ የማይታሰብ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው።

እርግጥ ነው! ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ተሸንሽኖ በሚሰጥ ግዛታችን ውስጥ የሚኖሩ ዜጎቻችን የህዝብን ቁጣ ላለመቀስቀስ ሲባል ለሱዳን በሚከለለው ግዛታችን ላይ እንዲቆዩ ሊደረግ ይችል ይሆናል። ይህ ግን የሉዓላዊነታችንን መከበር

አያመላክትም። ብዙ እየተዘፈነለት የምንሰማው የቻርለስ ጉወይን (Charles Gwynn) ጥረትም ቢሆን የዶ/ር ወንደወሰን ተሾመ ጥናት እንደሚያስረዳው ኢትዮጵያን ያላሳተፈ ሱዳንን ያስገበረው የእንግሊዝ መንግሥት በራሱ ያካሄደው ጥናት ከመሆኑም በላይ፤ ቻርለስ ጉወይን ራሳቸው እንደመሰከሩት ዳር ድንበር አልተካለለም። ስለሆነም የዳር ድንበር መካለል ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ መደረጉ አስፈላጊና መደገፍ ያለበት ቢሆንም፤ ድርድሩ ሚዛናዊ እንዲሆን መጀመርያ የኢትዮጵያ ገዢዎች ራሳቸውን ለኢትዮጵያ ጥቅም ያስገዙ መሆናቸውን ሊያረጋግጡልን ይገባል።

ከላይ እንደተገለፀው ይህ ፀሐፊ ለጊዜው የኢትዮ-ሱዳን ዳር ድንበር የማካለልን ጉዳይ በሚመለከት ብቁ መረጃ ያላሰባሰበ በመሆኑ፤ ሰፋ ያለ አስተያየቱን በይደር ይዞታል። የነገውን ለመቃኘት የትላንትናውን መለስ ብሎ ማየት ተገቢ መስሎ ስለታየው በዚህ ፅሑፍ ውስጥ የኢትዮ ኤርትራን የድንበር ውዝግብና የህወሓት/ኢህአዴግ ቋም በውዝግቡ ዙርያ ለመቃኘት ይሞክራል።

እንደሚታወቀው የኢትዮ ኤርትራ የድንበር ጦርነት የተጀመረው እ.ኤ.አ ግንቦት 6 ቀን 1998 ዓ.ም ሻዓቢያ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት በወታደራዊ ኃይል ሲወር ነው። ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ ጉዳይ መሆኑ ቀረና የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ አካል ገና ከመወረራችን በፊት ሻዓቢያ ይወረናል አይወረንም በሚል እሰጥ አገባ ክርክር ውስጥ ተጠምዶ ረዘም ላለ ጊዜ መቆየቱ ይታወቃል። ቢሆንም አቶ መለስ የመወረራችን መርዶ "ለፓርላማ" ያቀረቡትና "ፓርላማውም" ወረራው መቀልበስ አለበት የሚል አቋም የወሰደው እ.ኤ.አ በግንቦት 13 ቀን 1998 ዓ.ም እንደነበረም ይታወሳል።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ቁምነገር ሻዓቢያ ወረራ ከመፈጸሙ አስቀድሞ የድንበር አከባቢ ነዋሪ ህዝባችን ሻዓቢያ ኢትዮጵያን ሊወር በመዘጋጀት ላይ ነው የሚል እሮሮ በተደጋጋሚ ሲያሰማ መቆየቱ ነው። ይህንንም ተከትሎ የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ አካል አገርን የመከላከል ግዴታ እንዳለበት ተሰምቶት ሳይሆን፤ የህዝቡን እሮሮና አቤቱታ አስገድዶት ለብቻው እየተሰበሰበ ሻዓቢያ ይወረናል አይወረንም በሚል ጉንጭ አልፋ ክርክር ውስጥ ተጠምዶ እንደነበረ ይታወቃል። ባይሆን አንድ የአገር ሓላፊነት የተሸከመ መንግሥት ህዝብን በመቅደም፤ አገርና ህዝብ ከጥፋት ለመታደግ እንዲችል፤ ልዩ ልዩ መዋቅሮችን ዘርግቶ ጠላትን የመመከቻ ዜዴዎች አዘጋጅቶ መጠበቅ በተገባ ነበር። የኛ ሁኔታ ግን ልዩ ነውና፤ ህዝብ ልንወረር ነው፤ የመንግሥት ያለህ በሚልበት ጊዜ ሰሚ ጆሮ በማጣቱ በሻዓቢያ ይወረናል አይወረንም ክርክር ተጠምዶ የሰነባበተው የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ "ሻዓቢያ ሞኝ አይደለም" አይወረንም ይወረናል የሚሉ ሁለት ሓሳቦች ለድምጽ ቀርበው 5 ለ4 በሆነ ድምጽ አይወረንም የሚለው አቋም ማሸነፉንም ዘገይቶ መሰማቱ ይታወሳል። ሻዓቢያ ሞኝ አይደለም፤ አይወረንም ከሚሉት ወገኖች ውስጥ አቶ መለስ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንደነበሩም ሰምተናል። ይህ ቡድን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በወሰደው የተሳሳተ አቋም ተዝናንቶ ህዝብንና አገርን ለመዓት ዳርጓል። ይባስ ብሎም የሻዓቢያ አይወረንም ሰባኪ ወገኖች አብዛኞቹ ምንም ሳይነኩና ያለ ምንም ተጠያቂነት እስካሁን ያኔ በነበሩበት የሥልጣን ማማ ላይ እንደተቆናጠጡ ናቸው። በአንጻሩ በነዚህ መሪዎች ግድየለሽነትም እንበለው አውቆ አበድነት ምክንያት፤ ልንወረር ነው፣ የመንግሥት ያለህ! እረ ድረስልን በማለት እሮሮውን ሲያሰማ የባጀው የገፈቱ እንጂ የጥቅሙ ተቋዳሽ ሆኖ የማያውቀው ወገናችን፣ ዳር ድንበሩን ለመከላከል ውድ ህይወቱን ገብሯል። ከቀየው ተፈናቅሏል። ቤት ንብረቱን አጥቷል። መጨረሻውም ሕወቱን፣ ቤት ንብረቱንና ሰብአዊ ክብሩን ገብሮ በጦር ሜዳ ተፋልሞ ወረራውን ቢቀለብስም፣ አሁንም በነዛ ትላንት እሮሮውን አላዳምጥ ያሉ ወገኖች አይከፍሉ እዳ ከፍሎ በጦር ሜዳ ያገኘው ድል አልጀርስ ድረስ በመጓዝ ፈቅደው፣ ፈርሞው ባቋቋሙት የግልግል ዳኝነት አማካኝነት መስዋእትነቱ መና እንዲቀር ተደርጓል። በዚህም "መበደሉንማ ጌቶች በድሏል፣ መቀጣቱን ግን ባላገሩ ይቀጣል" የሚለው ቢህል ተግባራዊ ሆኗል። ነገሩ በዚሀ አላበቃም። ዛሬ መረጃዎቹ ግልጽ ወጥተው ሁሉም የሚያውቃቸው ቢሆኑም በሥራ አስፈጻሚው በሚስጥር እንዲያዝ የተደረገውና አሁን አቶ አስገደ በጋህዲ ቁጥር ሁለት ላይ ይመስለኛል በህወሓት ሥራ አስፈጻሚ አካላት መካከል "ሻዓቢያ ይወረናል፣ አይወረንም" ክርክር ጊዜ ሊወረን ነው የሚሉ ወገኖች አምርረው በመከራከራቸው፣ ያገር መከላከያ ኃይል በጉዳዩ ዙርያ ጥናት እንዲያቀርብ ተወስኖ ያቀረበው ጥናት ሻዓቢያ ኢትዮጵያን ለመውረር በመዘጋጀት ላይ መሆኑን የሚያሳይ እንደነበረ አስነብበውናል። ሆኖም አመራሩ የመከላከል እርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ አልነበረም። ኤርትራን በሚያዋስኑ ሉዓላዊ ግዛቶቻችን ውስጥ የሻዓቢያ መደበኛ ሠራዊት ግብረ-ኃይሎችን የመመከት ሓላፊነት የተጣለው ሙሉ በሙሉ በአከባቢው ህዝብና ምልሻ ተከሻ ላይ ነበር። ገዥዎቻችን አልጋቸው ላይ ተንጋለው ሲያንኮራፉ፤ ምልሻና ህዝብ የምደርስላቸው አጥተው ታንክና መትረየስ ታጥቆ ከመጣ ወራሪ ጠላት ጋር ጎሮሮ ለጉሮሮ ተናንቀው ተዋድቋል። ለዚህም እንደ አብነት በተለምዶ "የሰንበት ታጣቂዎች" በመባል የሚታወቁት የኢሮብ አርበኞች ዓይጋ ላይ ያሳዩት ጀግንነትና የከፈሉት መስዋእትነት እንደ አብነት የሚጠቀስ ሲሆን ጀግንነታቸውም ለዘላለም የሚዘከር ይሆናል። ውድ ህይወታቸውን የገበሩለት ሉዓላዊ ግዛታችን ግን በሸፍጥ ለሻዓቢ ተለግሷል። እነሱ ግዳጃቸውን ተወጥተው አልፈዋል። ሳይመለሱ አሸልቧል። አደራቸውን የመቀበል ግዳጅ ግን በሕይወት ባለነው ትከሻ ላይ ተጥሏል። ምርጫውም የኛ ይሆናል።

እዚህ ላይ ወረራውን አስመልክቶ "ፓርላማ" እንዲቀለበስ እንደወሰነ፤ አቶ መለስ በአንድ ወቅት የሰጡት መግለጫ ልብ ሊባል ይገባል። የኸውም፣ "ሳናውቀው ወዳጆቻችን ከኋላችን ወጉን" "they stubbed us from the back" የሚለው ነው። እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው የህወሓት ሥራ አስፈጻሚ የእንወረራለን አንወረርም ክርክር ሲያካሂድ፣ ህዝቡ የድረሱልኝ

እሮሮ ያስተጋባ እንደነበረ የሚያስረዳ በመረጃ ዛሬ በግልጽ ወጧል። የመከላከያ ደህንነት ክፍል፤ ሻዓቢያ እንደሚወረን የሚያረጋግጥ መረጃ ገና ከወረራው በፊት በአቶ መለስ ጠርጴዛ ላይ ተንጣልሎ እንደነበር ታውቋል። የአቶ መለስ ንግግር ከእውነት የራቀ እንደነበረ የሚያጠያይቅ አይደለም። ጦርነቱ እንደቆመ አቶ መረሳ ረዳ የተባሉ የባድመ፣ የሽራሮ፣ የዓዲሃገራይና የዓዲ አውዓላ አከባቢ የህዝብ ተወካይ "ነገር ግን ይህ ተንኳሽ የሆነ እንቅስቃሴ ለመጀመርያ ጊዜ ነው ማለት አይቻልም የቆየ ነው። ተቃውሞም ይገጥም ነበር። ሰሚ ግን አልነበረም። በኢትዮጵያ መንግሥት በኩልም አንድ ነገር እንዲደረግ እንጠቁም ነበር። ጉዳዩ በሰፊው ተይዟል የሚል መልስ ነበር የሚሰጠው።" ያሉት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዝያ 12 ቀን 1990 ዓ.ም እትም ላይ አትሞት ይገኛል። እኚህ የህዝብ ተወካይ ከሰጡት ቃለ-መጠይቅ የምንረዳው አቶ መለስ እንደነገሩን የሻዓቢያ ወረራ የማይጠበቅና የማይታወቅ ስዉር እንዳልነበረ ነው። አቶ መረሳ ረዳ በዚህ ቃለ-መጠይቅ ውስጥ የሚወክሉት ህዝብ አስቀድሞ ሻዓቢያ ሊወረን በመዘጋጀት ላይ ነው ብሎ ያስጠነቅቃቸው እንደነበረ ከማብራራታቸውም በላይ፣ ይህንን የህዝብ መልእክት በወቅቱ ለመንግሥት ያሳውቁ እንደነበር አረጋግጧል። ይህ ማብራርያቸውም እዚህ ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ያጠናክራል። አንባቢ ይህንን የአቶ መለስ "ሳናውቀው ተወረርን" አነጋገር አጣጥመህና መርምረህ የራስህን ፍርድ ስጥበት።

የሆነ ሆኖ ይህ ፀሐፊ ከላይ ያጣቀሳቸው መረጃና ማስረጃዎች የአቶ መለስን "ሳናውቀው ተወረርን" ማብራርያ ይቃረናሉ። አቶ መለስ እንደምንወረር አሳምረው ያወቁ እንደነበርም በግልጽ ያሳያሉ። ሆኖም ግን አቶ መለስን ማን ይጠይቃቸው? የግንባሩም፤ የፓርላማውም፤ የአስፈጻሚውም፤ የሕገ-መንግሥቱም፤ የአገር መከላከያ ኃይል አዛዥነቱም፤ የሁሉም ኮርማ ራሳቸው ናቸው።

ባይሆን ኖሮማ! አራት ኪሎ ቤተ-መንግሥት ውስጥ የተቀመጠ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር አገር ሲወረር ካላወቅክ የምትመራው መንግሥት አገር የመምራት ብቃት ስለሌለው ሁኔታው በፓርላማው አካል ወይም ሌላ ፓርላማው በሚቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ተጠንቶና ተጣርቶ እስኪቀርብ ድረስ ሥልጣንህን ታስረክባለህ ሊባሉ በተገባ ነበር። አገር ሲወረር ምን ትሠራ ነበር? አገር ተወሮ ወገን ላይ ግፍና ሰቆቃ ሲደርስ ሊታውቅ ያልቻልክበት ምክንያት ምንድ ነው? ተብለው ሊጠየቁና አጥጋቢ መልስ ይዘው ለመቅረብ ካልቻሉ፣ በሕግ ሊከሰሱና ሊፈረድባቸው በተገባ ነበር። አራት ኪሎ ቤተ-መንግሥትም ሆነ በሌላ የህዝብ ሥልጣን የሚቀመጥ ሰው በየደረጃው እንደየ ሥልጣን እርከኑ ላጠፋው ጥፋት ተጠያቂ መሆን ይኖርበታልና መጠየቅ ነበረባቸው። በህዝብና በአገር ህልውና ላይ ሊቀለድ አይገባም። ይህ ጉዳይ ለወደፊት ሥልጣን ላይ የሚወጡ ወገኖች ጥሩ ትምህርት ሊማሩበት በሚገባ መልኩ መቋጨት ነበረበት።

ለመሆኑ አንድ ዜጋ የህዝብን ሥልጣን ይዞ ቤተ መንግሥት ውስጥ እንዲኖር የሚደረግበት ምክንያት ምንድነው? የዘመኑ ነገር አይታወቅምና ጥፋተኞችን የመሸለም አዲስ ባህል እየተፈጠረ ካልሆነ በስተቀር፤ የአገርና ህዝብን ደህንነት ከመጠበቅና ማስጠበቅ ውጭ ቤተ-መንግሥት ውስጥ የሚያስመሽግ ሌላ ተግባር ሊኖር አይችልም። ስለሆነም የአገር መሪ ሆነው ቤተ-መንግሥት የሚቀመጡት መከበር ባለባቸው ጊዜ እንደሚከበሩ ሁሉ መጠየቅ ባለባቸው ጊዜ መጠየቅ አለባቸው። አቶ መለስ "ሳናውቀው ተወረርን" ብለውናል። አንድ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ቢኖር ግን "ሳያውቁትም" ሆነ አውቀውት አገርና ህዝብ መወረር የለባቸውም። በመሆኑም እንዴት ነው ነገሩ? መባል ነበረባቸው፣ አለባቸውም። የአገርና የህዝብ ጉዳይ ጊዜ ይወስዳል እንጂ አያረጅምና አሁንም መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የተዘጋ ፋይል ነው ሊባል አይገባም። የዛሬ የአቶ መለስ መጠየቅ ለነገዎቹ ባለሥልጣናት መማርያ መሆን መሆን አለበት። ካልሆነ ግን ባገራችን ውስጥ ሥልጣን የጨበጠ ሁሉ የፈለገውን የማድረግ መብት እንዳለው ተደርጎ የመቆጠር አደጋን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ደግሞ ህዝብ ለዘለቄታው በመንግሥት ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደርጋል። ህዝብ እምነት ያልጣለበት መንግሥት የፈለገውን ያህል ቢጥር፤ ዳገትና ቁልቁለት ቢወጣ ቢወርድ ድምር ውጤቱ ዜሮ ሊሆን እንደሚችል መገመት ብልህነት ይሆናል። አቶ መለስና የሚመሩት አገዛዝም ሆነ ፓርቲ አሁን የወደቁበት ማጥ ውስጥ የተዘፈቁት ህዝብ አመኔታ ስለነሳቸው እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

እስካሁን ድረስ አቶ መለስ "ሳናውቅው" ተወረርን በማለት የነገሩን ትክክል እንዳልነበረ ለማስጨበጥ ተሞክሯል። ማስረጃዎቹም ይፋ የወጡ በመሆናቸው ለማየትና እውነቱን ለማግኘት የፈለገ ሁሉ አይቶዋቸዋል፤ ሊያያቸውም ይችላል። ይህ ደግሞ አቶ መለስ የሚነግሩን ሁሉ እውነት እንዳልሆነ ለመገንዘብ ያስችለናል።

ነገሩ በዚህ አላበቃም። ሻዓቢያ ዳር ድንበራችንን ወሮ ህዝባችንም እንዳለ ከቀያው ተፈናቅሎ፣ የወገን ምልሻ ከጠላት ኃይል ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ትንቅንቅ ተያይዞ ሲዋደቅ፣ እንደ ዛላንበሳ የመሳሰሉ ከተሞቻችን ወደ አፈርነት ሲለወጡ፣ የዓይደር ህፃናት ከሻዓቢ አየር ኃይል በተጣለ ክላስተር ቦምብ ሲጨፈጨፉ፣ ዓዲግራት ውስጥ በሻዓቢያ ወረራ ምክንያት የተፈናቀለው ህዝባችን ሰብአዊ እርዳታ ለማግኘት በተሰለፈበት ቦታ ላይ የሻዓቢያ የአየር ድብደባ ሰለባ በሆነበት፤ አቶ መለስና የሚመሩት ቡድን ራስን የመከላከል ጦርነት እንዳይካሄድ ይከላከሉ እንደነበር አቶ አስራት አብርሃም "**<u>ከአገር በስተጀርባ</u>** ህወሓትና ሻዓቢያ - የትሮይ ፈረስና የባለፈረሱ ተልእኮ" በሚል ርእስ ባሳተሙት ግሩም መፅሓፋቸው ገጽ 115 ውስጥ የአቶ ቴድሮስ ሐጎስን ቃለመጠይቅ በመጥቀስ እንደሚከተለው አስፍረውት ይገኛል።

> “እኛ ሻዓቢያ ቢወረንም ችግር የለውም። ዝም ብለን ልማታችን ብቻ እንቀጥል፤ ሻዓቢያ ስንት ዓመት እንዳይኖር ነው ስንላቸው፤ እነስዬ ግን ጦርነት ለማድረግ ስለፈለጉ ‘ሻዓቢያን እዚህ የነበረችውን ድንጋይ አንስተሃል፤የነፋሱን አቅጣጫ እንዲቀየር ከሰሜን ወደ ደቡብ ‘እንዲፈስ’ አድርገሃል፤ ሌላም ሌላም ምክንያት ፈጥረን እንምታው’ይሉ ነበር። የትምክህተኞች ሀሳብ በማምጣትም ‘አሰብን በሃይል እንያዝ፤ ሻዓቢያን እንገርስሰው’ይሉ ነበር;; ይህን ጦርነት እንዲካሄድ የፈለጉበት ምክንያትም በጦር መሳርያው ግዢ ሰበብ በግላቸው ለመጠቀም ይፈልጉ ስለነበር ነው;; ለምሳሌ ስዬ በራሱ ጊዜ ገንዘብ በሻንጣ ተሸክሞ ወደ ውጭ ይመላለስ ነበር።”

ከዚህ ከአቶ ቴድሮስ መልስ የነአቶ መለስ ቡድን የኢትዮጵያን ሉዓላዊ መሬት ለወራሪው ሻዓቢያ ያለምንም ውጣ ውረድና ቅድመ-ሁኔታ ለመስጠት አስቀድሞ ተዘጋጅቶ እንደነበረ ነው የሚያመላክተው። “.......ሻዓቢያ ስንት ዓመት እንዳይኖር ነው ስንላቸው፤ እነስዬ ግን ጦርነት ለማድረግ ስለፈለጉ.....” የሚለው ስንኝ የነአቶ ቴዎድሮስ ሐጎሰና የነአቶ መለስ ዜናዊን አርበኝነትና ለአገር ተቆርቋሪነትና ቀናኢነትን የሚያመላክት አይደለም። እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ሻዓቢያ የስንት ዓመት ዕድሜ ይኖሯል? ወይም እነስዬ ጦርነት ለማድረግ ፈልጓል የሚል አይደለም። የሚነሳው መሥረታዊ ጥያቄ ሻዓቢያ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት መውረሩን የመቀበልና ያለመቀበል ጥያቄ ነው የሚሆነው። ይህንን መስፈርት አስቀምጠን ስንቃኘው ደግሞ ቢያንስ የእነ አቶ ቴዎስሮስ ሓጎስና አቶ መለስ፣ አቶ ስብሐት ቡድን ሻዓቢያ ሉዓላዊ ግዛታችንን ወሯል ብለው እንደማያምኑ ከአቶ ቴዎድሮስ ቃለመጠይቅ ለመረዳት ይቻላል። ይህም ማለት ሻዓቢያ ጦርነት የከፈተባቸው ግዛቶች የኤርትራ ግዛቶች ናቸው ብለው ያምናሉ የሚለው ድምዳሜ ላይ እንድንደርስ ያስገድደናል። ባይሆን ኖሮ፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከቤቱ፣ ንብረቱና አከባቢው ተፈናቅሎ የሚቀመስ አልባ በመሆን በየዋሻውና ጣሻው በመንከራተት ላይ ባለበት ሁኔታ “ሻዓቢያ ስንት ዕድሜ እንዳይኖረው ነው” ብሎ ወረራው እንዲቀጥል ሙግት አያነሱም ነበር። ለመሆኑ፤ እነዚህ ሰዎች የዓይደር ትምህርት ቤት ህፃናት እልቂት ምንም አልተሰማቸውም? ዓዲግራት ከተማ ውስጥ በወረራው ከተፈናቀለው ህዝብ ጉልበት ያለው ደርሶ እርዳታ እንዲሰጠው በሚጠብቅበት የእርዳታ ማከፋፈያ ማእከል ላይ በተጣለው የአይሮፐላን ቦምብ ላለቁ ወገኖች ስሜት አልነበራቸውም? ከግማሽ በላይ የሚሆነው የኢሮብ ህዝብ በሻዓቢያ ወረራ ምክንያት አከባቢውን ለቆ መሰደዱ ለማንም የተደበቀ አልነበረም። ከዛም በላይ ሻዓቢያ በወረረው ግዛት ውስጥ ያገኛቸው መኖክሲቶችና ካህናት እንኳ ሳያስቀር የኢሮብ ዜጎችን ታጋች (hostage) አድርጎ ወስዷቸው ነበር። ከነዚህም ውስጥ ከ100 በላይየሚሆኑ ዜጎች እስከ ዛሬ ድረስ የደረሱበት አይታወቅም። የነዚህ ዜጎች እጣ ፈንታ አስጨንቆት፤ አንድ መግለጫ እንኳ ስለነሱ ከአገዛዙ በኩል የወጣ የለም። ይህ ሁሉ ተደማምሮ ሲታይ ዳር ድንበራችን ለሻዓቢያ ለመለገስ አንድ የተቀነባበረ ውዲት እንዳለበት ከምን ጊዜውም በላይ ዛሬ ግልጽ ሆኖ ታይቷል።

በተጨማሪም፤

> “እነስዬ ግን ሻዓቢያን እዚህ የነበረችውን ድንጋይ አንስተሃል፤የነፋሱን አቅጣጫ እንዲቀየር ከሰሜን ወደ ደቡብ እንዲፈስ አድርገሃል፤ ሌላም ሌላም ምክንያት ፈጥረን እንምታው’ይሉ ነበር።” ይላሉ።

ይህ አገላለጽ አቶ ቴዎድሮስና የሚወክሉት ቡድን ሻዓቢያ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች ወረዋል ብለው እንደማያምኑ ያመላክታል። በመጨረሻ በግልግል ዳኝነት ተገኘ የተባለውና ከአንድ ሶስተኛ በላይ የኢሮብ መሬትን ለሻዓቢያ ያስረከበው ብይን የሚመነጨውም ከዚህ አመለካከትና እምነት ይሆናል። ይህ ፀሓፊ በዚህ አገዛዝ ላይ እምነት እንዲያጣ ያደረገውም ይህ የነአቶ ቴዎድሮስና የሚወክሉት ቡድን አቋም ነው። በመሆኑም አቶ ስዬ፣ በአቶ ቶዎድሮስ እንደተነገረን “ በራሱ ጊዜ ገንዘብ በሻንጣ ተሸክሞ ወደ ውጭ ይመላለስ ነበር” የሚለው ከሻዓቢያ ወረራ ጋር የሚገናኝ አይደለም። አቶ ስዬ ገንዘብ በሻንጣ ተሸክሞ ይመላለስ አይመላለስ የሻዓቢያን ወረራ ለመቀልበስ የወሰደው አቋም ሓላፊነት የተሞላበትና ከአንድ ኢትዮጵያዊ መሪ የሚጠበቅ ነው። ሻዓቢያ የወረረው ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛት ነው። ከቀያው ያፈናቀለው፣ የፈጀውና እስከዛሬ ድረስ የደረሱበት ያልታወቀው አግቶ የወሰዳቸው ዜጎች ኢትዮጵያዊያን ናቸው። ስለሆነም፣ ሻዓቢያ መመታት የነበረበትና የተመታውም አቶ ቴዎድሮስ ሊሞግቱን እንደሞከሩት ድንጋይ በማንሳቱ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት ወሮ በመያዙ ነው። የተቀበሩ ውሎችን አውጥቶ እንዲሞግት በመስማማትና በግልግል ፍርድቤቱም ፊት ኢትዮጵያን የሚጎዳ ምስክርነት በመስጠት የሻዓቢያ ተባባሪ መሆናቸውን ያስመሰከሩት እነአቶ ቴዎድሮስ ሐጎስና ላኪዎቻቸው መሆናቸው የሚታየውም እዚህ ላይ ነው።

የግልግል ዳኝነቱ ውሳኔ ቁጥር 4.69 እንደሚከተለው ይላል፤

> “ ...........ኢትዮጵያ የተጠቀመችባቸው ቃላቶች እነዚህ ነበሩ“ ፎርት ካዶርኖ፣ ሞኖኰሰይቶ፣ ጉናጉናና ፆሮና በአብዛኛው ጥያቄ ያልተነሳባቸው የኤርትራ ቦታዎች ናቸው።” The words used by Ethiopia were that”Fort Cadorna, Monoxeito, Guna Guna and Tserona”were “mostly.....undisputed Eritrean palaces>” ይልና። ቀጥሎም፣ በቁጥር 4.70 ፆሮናን በሚመለከት ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ በጽሑፍ የሰጠችውን የእምነት ቃል መሠረት በማድረግ መተግበሩን ችላ ማለት አይችልም። ኮሚሽኑ የኢትዮጵያን የእምነት ቃል ግምት ውስጥ

> ለማስገባት ይገደዳል። በመሆኑም የውሉን መስመር ኤርትራ ግዛት ውስጥ እንዲካተት ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።" "As to Tserona the commission cannot fail to give effect to Ethiopia's statement, made formally in a written pleading submitted to the commission. It is an admission of which the commission must take full account. It is necessary, therefore, to adjust the Treaty line so as to ensure that it is placed in Eritrea territory." እንግሊዝኛው የኮሚሽኑን ቃል እንዳለ ለመረዳትና ግርድፉን ትርጉም ላለማዛባት የተጨመረ ነው።

እንግዲህ አንባቢ የአቶ ቴዎድሮስ ሐጎስን ቃለ-መጠይቅ ከዚህ ከኮሚሽኑ ውሳኔ አንፃር ከፈተሸው እውነቱን ለመረዳት እንደሚችል ጥርጥር የለውም። እ.ኤ.አ በ1900 ዓ.ም በኢትዮጵያና ጣሊያን መካከል ተፈጸመ የሚባለው ውል ፆሮናን በኢትዮጵያ ውስጥ ያካተተ እንደነበረ ኮሚሽኑ ቢያረጋግጥም ኢትዮጵያ የማያከራክር የኤርትራ ግዛት ነው ብላ በጽሑፍም በቃልም ስላረጋገጠች ኤርትራ ውስጥ እንዲትካተት ከመወሰን ውጭ ሌላ አማራጭ እንዳልነበረው ብይኑ ውስጥ አስፍሮት ይገኛል። መረጃውም ማስረጃውም ይኸው ቀርቧል። ከዚህም በመነሳት እነአቶ መለስ ለዳር ድንበራችን መከበር የሚያሳዩት ቀናኢነት አስተማማኝ እንዳልሆነ ለመገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ዛሬም ቢሆን ዳር ድንበራችን ለመከበሩ ምንም ማስተማመኛ የለም። መረጃዎችም የሚያሳዩን ጥርጣሬአችንን የሚያጠናክር እንጂ የሚቀርፍ ባለመሆኑ ዜጋ በተጠንቀቅ ቆሞ "ሄግ በተወሰነው መሠረት" እየተባለ ዳር ድንበራችን ለባዕድ እንዳይሰጥ መከላከል እንደሚገባው ለማስገንዘብ ነው።

የኢህአዴግ አመራር ለኤርትራ (ለሻዓቢ ቢባል ይሻላል) ጥቅም አስከባሪነት መቆሙን ለማሳየት የመረጃና ማስረጃ ብዛት እንጂ እጥረት የለም። የተለያዩ የግል ጥቅማጥቅሞችን በማሳደድ ላይ ለሚገኙ ወገኖች ይህ ቁልጭ ብሎ የወጣ ሃቅንም ለመዋጥ እንደሚቸገሩ የታወቀ ነው። እነዚህ ወገኖቻችን ጋር ለወደፊት ሰከን ብለን የምንከራከርበት ሁኔታ ይኖራል። ለጊዜው ግን የነአቶ መለስ ቡድን ወዶና ፈቅዶ ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን ለሻዓቢያ ያስረከበበትን ጉዳይ የትችቱ ማእከል አድርጎ ለመቀጠል ተመርጧል። በመሆኑም፣ አቶ ስዬ አብርሃ "ነፃነትና ዳኝነት በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ገጽ 274 ላይ የሚያቀርቡትን ቀጥለን እንመልከት፤

> ".......በአቶ መለስ በኩል የነበረው ሁኔታ አጥጋቢ ያልነበረ ቢሆንም በቀጥታና በግልጽ መጋጨት የጀመርነው ታህሳስ/ጥር 1991 አከባቢ በማእከላዊ ኮማንድ ስብሰባ ላይ የውግያ አይሮፕላን መግዣ ገንዘብ አስፈልጎ፣ የራሳችን ገንዘብ እንጠቀም በሚባልበት ጊዜ ይህ ገንዘብ የኛ ቢሆንም እንዳንነካው አይ ኤም ኤፍ ገደብ የጣለበት ስለሆነ ልንነካው አንችልም ብለው በተከራከሩበት ወቅት በበኩሌ ጉዳዩ ከሀገር ሉአላዊነት ማስክበርና ከአይ ኤም ኤፍ ጋር ተገባ የተባለውን ስምምነት ከማክበር መካከል የትኛውን እናስቀድም ብሎ የመምረጥ ጉዳይ እስከሆነ ቅድምያ ለሀገር ሉአላዊነት ማስከበር ሰጥተን የሚፈለገውን ገንዘብ ወጪ አድርገን እንግዛ በሚሉት ሐሳቦች ተለያይተን በተከራከርንበት ጊዜ ነው።"

እንግዲህ አገር ተወሮ ዜጎች የመንግሥት ያለህ የሚሉበት ወቅት ላይ እንደነበረ ልብ እንበል። አይ ኤም ኤፍ ለኢትዮጵያ በእርዳታም እንበለው በብድር ገንዘብ ሰጥቶ፤ አገዛዙ ተረክቦ ካዝና ውስጥ ቆልፎት እንደነበረ የሚዘነጋ አይደለም። ወቅቱ ደግሞ አገር ተወሮ፤ ወገን ተሸብሮ የመንግሥት ያለህ እያለ የድረሱልኝ እሮሮውን እያስተጋባ የነበረበት ነው። ታዲያ! ይህ ገንዘብ አገርንና ህዝብን የመታደግ ዓላማ ላይ ካልዋለ ለኢትዮጵያ ምኑን ነው የበጃት? በዛን ወቅት ከዛ የባሰ ችግር ገጥሟት ነበር? አቶ ኢሳያስ እንዳሰበው በለስ ቀንቶት "ኢትዮጵያን ቢቆጣጠር" ኖሮ የዛ ገንዘብ ፋይዳ ለኢትዮጵያዊያን ምን ይሆን ነበርን? ነው ወይስ አስጊ ሆኔታ ቢፈጠር ተብሎ ለስንቅ ሊያዝ ስለታሰበ? እውነቱን ለመናገር ይህ ጉዳይ የሚገባ አይደለም። በመሆኑም፣ ባለፉት ነገሮች ላይ ከአቶ ስዬ ጋር ልዩነት ቢኖርም በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ዙርያ አቶ ስዬና ጓደኞቻቸው ያሳዩት አቋም ከአንድ ብቃት ካለው ላገርና ወገን ቀናኢ ከሆነ አመራር የሚጠበቅ ነበር። በአንጻሩ የነአቶ መለስ አቋም ከተሸናፊነትና "ከተንበርካኪነትም" የዘለለ የአገር ክህደትን ያንጸባረቀ ነበር።

ገንዘቡ ከየትም ይሁን ከየት እንዲህ ዓይነት አገርንና ወገንን የሚያጠፋ የባዕድ ወረራ ሲከሰት ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። ለዚህም ጠ/ሚኒስትሩ ደንቃራ መፍጠር ባልተገባቸው ነበር። በመሆኑም አቶ መለስ ገንዘቡን ወጪ አላደርግም ማለታቸው ሻዓቢያ የወረራቸውን ሉዓላዊ ግዛቶቻችን ይዞ ዜጎቻችንን እንደፈለገ እያበሳበሰና እያንገላታ ይፈንጭበት የሚል ውሳኔ ከመውሰድ ውጭ ተደርጎ የሚታይ አይሆንም። አገር ከሌለ አይ ኤም ኤፍ የለገሰን ገንዘብ ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ነው አቶ መለስና ተከታዮቻቸው የወሰዱት አቋም በአገር ላይ እንደተዶለተ ክህደት የሚቆጠረው። አቶ ቴዎድሮስ እንደነገሩን ሻዓቢያ ለስንት ዘመን እንዳይቆይ ነውና፤ ተውቱ በወረራ የያዘው ግዛታችን ውስጥ ይንገዋለልበት የሚል መልእክት ከማስተላለፍ ውጭ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚቻል አይሆንም። ይህ ደግሞ ምናልባት በአቶ ቴዎድሮስ አንደበት በመደገሙ እንደ አዲስ አቋም አድርገን ካልተመለከትነው፤ ገና ወረራው ከመቀልበሱ በፊት በሕወሓት ሥራ አስፈፃሚ አካል ስብሰባ ወረራውን እንዴት ማስተናገድ እንዳደሚገባ ሲከራከሩ፤ አቶ ስብሐት ነጋ "ሻዓቢያ ዛላንበሳን ለ20ና 30 ዓመት ቢይዛት ምንድነው ችግሩ" በማለት መከራከራቸው ሁላችን የሰማነው ሃቅ ነው። አገር በወረራ ሥር በነበረበት ሁኔታ አገርን ለመከላከል የሚያስፈልገውን ገንዘብ የማፈላለግና የማግኘት ሓላፊነት ከሁሉም በላይ የጠቅላይ

ሚኒስትሩ መሆን በተገባው ነበር። የአይ ኤም ኤፍ ገንዘብ አይነካም ከተባለ ሌላ አማራጭ የገንዘብ ምንጭ መኖሩንም ማረጋገጥ የነበረባቸው እሳቸው ናቸው። ካልተገኘ ግን በምንም ይሁን በምን የአገርና የህዝብ ሉዓላዊነት መከበርና መጠበቅ ነበረበትና የአይ ኤም ኤፍ ገንዘብ አገርን የመከላከል ጥቅም ላይ መዋል ነበረበት። ጠ/ሚኒስትሩ አገር ተወሮ ገእያለ ንዘብ ውጪ አይደረግም ብለው መከራከራቸው አስነዋሪ ነው። በመሆኑም፤ ይህ ተግባራቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወራሪ እንዲሸለም መፍቀዳቸውን ያሚያሳይ ይሆናል። ክስተቱም የዚህ ትውልድ የታሪክ ጠባሳ ሆኖ በታሪካችን ውስጥ ይመዘገባል።

አቶ ስዬ በገጽ 283 ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፤

> "…. የእርሳቸው መንግሥት ግን (የአቶ መለስ ማለት ነው)የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለኤርትራዊያን ነጋዴዎች ገንዘብ ክፈሉ የሚል አስገዳጅ ስምምነት እንዲገባ በማድረግና በዚሁም ምክንያት ከአንድ ቢልዮን ብር በላይ የሀገሪቱ ሀብት ተዘርፎ እንዲቀር አስገድዷል።"

እንግዲ ኢትዮጵያ በካዝናዋ ያለውን ገንዘብ ለሉዓላዊነቷ መከበር ወጪ ማድረግ የለባትም የሚሉት አቶ መለስ የሻዓቢያን ጦርና ጦረኝነት ለማጠናከር ምን ያህል እንደሰሩ ከአቶ ስዬ ጥቅስ ለመገንዘብ ይቻላል። ሻዓቢያ ኢትዮጵያ ውስጥ በግለሰብ ኤርትራዊያን ስም ምን ዓይነት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አሻጥር ይፈጥር እንደነበረ እንኳን አቶ መለስ እኛ ተራ ዜጎችም በገሃድ የምናየው እውነት ነው። የነበረውን ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብተን ከመረመርነው፤ ይህ ለኤርትራ ነጋዴዎች ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በቀጥታ ሻዓቢያ እጅ ገብቶ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ኤርትራ በአዲስ አበባ የሻዓቢያ ኤምባሲ ውስጥ በሕገ-ወጥ መንገድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚፈቅደው ውጭ አንድ የአሜሪካን ዶላር በ7.25 ብር ሒሳብ ከመመንዘር ጀምሮ በዓለም ላይ 14ኛ ቡና አምራች አገር እስመባል ደርሳ እንደነበረም የሚታወቅ ነው። አቶ መለስ ኢትዮጵያ በካዝናዋ የተቀመጠውን ገንዘብ በጦርነት ለተደፈረው ዳር ድንበሯ መከላከያና በጀብደኞች ጦርነት ከቤት ንበረቱ ለተፈናቀለው ዜጋ የሕይወት ማቆያ እንዳይሆን የመከላከል ሙከራ አርጓል። በዚህም ሻዓቢያ ለከፈተብን እብሪተኛ ጦርነት ድጋፋቸውን ሰጥቷል። ይባስ ብሎም 70.000 በላይ ውድ የኢትዮጵያውያን ሕይወት የተገበረበት ሉዓላዊ ግዛቶቻችን ሄግ ድረስ በመጓዝ ሻዓቢ እንዲረከበው ተደርጓል። በዚህም ሻዓቢያ በገዛ በሀብታችንን ተጠቅሞ የወረረውን ግዛታችን ተለግሶለት ድል በድል ሲሆን፤ የሚቆምላት መንግ፤ስት የሌላት ኢትዮጵያ ግን በጦር ሜዳ የተቀዳጀችውን ድል በግልግል ፍርድቤት ከሳሽና ተከሳሽ ተብየዎች ግንባር ፈጥረውባት ተገፍታ ቀርታለች።

***<u>ወገን እንዳንዘናጋ!</u>***

ዛሬ ሊያዘናጉን የሚፈልጉ አንዳንድ ወገኖች "አቶ መለስ አምስት ነጥቦች አቅርቧል። ስለሆነም መንግስታችን ለሉዓላዊነታችን መከበር ቆርጦ ተነስቷል" እያሉ በማሞካሸት ላይ እንደሚገኙ የምንዘነጋው አይሆንም። በትግርኛ አንድ አባባል አለ። "ዓሻ መሲልካ ድራሮም ወድኤሎም" በግርድፉ ሲተረጉም ሞኝ መስለህ እራታቸውን ጨርስባቸው እንደማለት ነው። እነዚህ ወገኖች የሚናገሩትን በመረጃ የተደገፈ አይደለም። እንዲሁ በሌጣው እመኑን ሊሉን ይቃጣቸዋል። ሞኞች እንዳይባሉ ሞኞች አይደሉምና፤ ብልጣብልጦች ብንላቸው ይመረጣል። አቶ መለስ ነግረውናልና ሉዓላዊነታችን ተረጋግጧል የሚለው አባባል በአመክንዮ የተደገፈ አይደለም። ጊዜ ከፈቀደ አቶ መለስ አቀረቡት የሚባለው 5 ነጥብ የመደራደርያ ሀሳብ ሰፋ ባለ መልኩ ጊዜ ሲፈቅድ የሚተች በመሆኑ፣ ላሁን ራሳቸው አቶ መለስ እንደነገሩን "ሰጥቶ መቀበል" በሚለው ላይ የተንጠለጠለ ሉዓላዊነታችንን ለማረጋገጥ የሚያስችል ይዘት የሌለው ባዶ ለጊዜ ምግዣ የተወረወረልን ሓሳብ ነው ብለን እንለፈው። ምክንያቱም "ሰጥቶ ለመቀበል"፣ የሚሰጥ ሊኖርህ ይገባልና። ለመስጠት ደግሞ ኢትዮጵያ ከኤርትራ የወሰደችው ወይም እንድትወስድ የተወሰነላት መሬት የለምና የአምስቱ ነጥቦች ይዘት፤ በድርድር ስም የሄጉን ብይን ተግባራዊ እናድርግ ከማለት ያለፈ ትርጉም አይኖራቸውም። ጉዳዩ በኢህአዴግ ጓዳ ተቦክቶ፣ ተጋግሮ አልቋል። የኢትዮጵያን ጉዳይ እንደፈለገ በማድረግ ላይ የሚገኘው ህወሓት/ኢህአዴግ በራሱ ልሳን ያሰፈረው ሌጣ ሃቅ በብልጣብልጥ ተላላኪዎች ሊሻር አይችልም። ህወሓት/ኢህአዴግ ሉዓላዊነታችንን አስመልክቶ አቶ አስራት አብርሃም ከላይ በተጠቀሰው መፅሓፋቸው ውስጥ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ያሰፈረውን ከገጽ 150-151 እንደሚከተለው አስፍረውት ይገኛል።

> "ወረራውን የመመከት ጉዳይ የመሬት ጉዳይ አይደለም፤ ጉዳዩ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ አጉራ ዘለልነትን የማስወገድ ጉዳይ ነው በማለት መንግሥታችንና ድርጅታችን አድማጭ እስከሚሰለቸው ድረስ በተደጋጋሚና በወቅቱ መግለጻቸው የሚታወስ ነው። ይህ ማለት ግን ሁሉም ይህንን ዓላማ ተረድቶ ነበር ማለት አይደለም።አንዳንዶቹ ጉዳዩ የመሬት ጉዳይ ነው፤.......። የኤርትራ ነፃነት በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ እልባት ያገኘ ጉዳይ ነው። ትግላችን የህግና የሰላም እንጂ የመሬት ወይም የወደብ አይደለም። .........ስለዚህ ለኛ ባድመ ትልቅ ትሁን ትንሽ፤ ወርቅ ይኑራት አይኑራት ትርጉም የለውም።......ባድመን የሕግን የበላይነት ከማረጋገጥ አኳያ ባላት ፋይዳ እንጂ በመሬትነቷ አናያትም። .......መሬቴ ነው ስለዚህ ባለሁበት ሆኘ በሃይል የያዝኩት ቦታ ላይ ሆኜ ካልሆነ

> በቀር ለዳኝነት አልቀርብም ይል የነበረውሻዓቢያ በአጉራ ዘለልነት ያካሄደውን፤ የህግን የበላይነት በመጣስ የፈጸመውን ወረራ ቀልብሰህ ወደ ዳኛ ቅረብ ቢባል አሻፈረኝ ያለው ሻዓቢያ ድንበሩ እስኪወሰን ድረስ ሰራዊትህን ከወረራው በፊት ታስተዳድረው ከነበረው የኤርትራ ድንበር 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አስፍርና ወደ ዳኛ ቅረብ ሲባል እሬት እሬት እየመረረው ተቀብሎ ተፈራረመ። በዛን ወቅት እኛ ዓላማችን በማያዳግም ሁኔታ ተሳክቷል። ወረራው ተቀልብሷል። የድንበር ጉዳይ በህግ ይወሰን አልን። ....... ጥያቄያችን የህግ የበላይነት እንጂ የመሬት ስላልነበረ የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ድላችን እውን ሆነ።"

አቶ አስራት አብራሃም በመጽሐፋቸው ውስጥ ይህንን በአንደኛው የዓለም ጦርነት የጀርመን ሽንፈትና ድርድርን እንደምሳሌ በመጥቀስ ውብ አድርገው አብጠልጥለው ተችተውታል። ድርድሩንም "ከሽንፈት የማይሻል" ብለውታል። ይህ ፀሐፊ ደግሞ ከሽንፈት የማይሻል ሳይሆን የሽንፈት ሽንፈትም ጭምር ነው ይለዋል።

ይህ የኢህአዴግ ልሳን ያወጣው ሐተታ የሚያጠነጥነው አንድ መሠረተ ሓሳብ ላይ ነው። ይኸውም ጦርነቱ የተካሄደው የህግ የበላይነትን ለማስከበር እንጂ ሉዓላዊነትን ለማስከበር የተካሄደ ጦርነት አለመሆኑ ላይ ነው። "ባድመን የሕግን  የበላይነት ከማረጋገጥ አኳያ ባላት ፋይዳ እንጂ በመሬትነቷ አናያትም።" የሚለው አባባል በውስጠ ታዋቂነት ሁሉም የተወረሩ ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን የሚያካትት አገላለጽ ነው። ሆኖም ይህ የሚያከራክር አይሆንም። በጉልበት የተያዘብንን ሉዓላዊ ግዛታችንን የሚመለከት እስከሆነ ድረስ ሌሎች በወረራ የተያዙ ግዛቶቻችን በሐተታው ውስጥ መካተት አለመካተታቸው ብዙም ፋይዳ አይኖረውም። ችግሩ ያለው አስተሳሰቡና እምነቱ ውስጥ ነው። በኢህአዴግ ዐይን ለህግ የበላይነት መከበር እንጂ ለተወሰደብን መሬት ብለን አልተዋጋንም። ያ ሁሉ የጀግኖቻችን፣ የብርቅየዎች ሕይወት የተከፈለው "የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ነው" ተብለናል። ለዚህ ፀሐፊ ደግሞ ያ መከበር አለበት የሚባለው ሕግ የሚሠራው በመሬት ላይ ነው። የጦርነቱ ዓላማ አቶ መለስና ለሚመሩት ኢህአዴግ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ነው። በመሆኑም የጦርነቱ ዓላማ ላይ ተለያይተናል። ኢትዮጵያዊያን መተኪያ አልባ ሕይወታቸውን የሰጡት ለዳር ድንበሯ መከበርና የወገናቸውን ሰቆቃ ለመታደግ ነው። ባድመን ጨምሮ ሁሉም ከኤርትራ ጋር የሚዋሰኑ ግዛቶቻችን ላይ የጅብደኝነት ወረራ ባይካሄድብን ኖሮ የአንድም ሰው ሕይወት ባልጠፋ ነበር። ህግ የሚከበረው በሉዓላዊ ግዛት ውስጥ ነው። ሠራዊታችን ባድመ የዘመተው በሰላም አስከባሪነት ሳይሆን ሕይወቱን ገብሮ ሉዓላዊ ግዛታችንን ለማስከበር ነው። ይህ መብት ደግሞ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር ምዕራፍ 7 አንጽ 51 ላይ እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፡፡

## Chapter 7 article 51

> Nothing in the present Charter shall impair the inherent right of individual or collective self-defence if an armed attack occurs against a Member of the United Nations, until the Security Council has taken measures necessary to maintain international peace and security. Measures taken by Members in the exercise of this right of self-defence shall be immediately reported to the Security Council and shall not in any way affect the authority and responsibility of the Security Council under the present Charter to take at any time such action as it deems necessary in order to maintain or restore international peace and security.

በዚህ አንቀጽ መሠረት ኢትዮጵያ ራሷን የመከላከል ሙሉ መብት ቢኖራትም እነአቶ መለስ እንዳትጠቀምበት እንቅፋት ሆኖውባታል። ብልጣብልጦቹም ይህንን እያወቁ በአገርና በህዝብ ሰቆቃ የግል እንጀራቸውን (እጅ ለመንሳት ፈቃድ ለማግኘትም ሊሆን ይችላል) ለማብሰል ከሚያደርጉት ተራ አጭበርባሪነት ቢቆጠቡ ይሻላል። "ጥያቄያችን የህግ የበላይነት እንጂ የመሬት ስላልነበረ የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ድላችን እውን ሆነ።" ተብሎ ተደምድሟል። ውጤቱንም አይተነዋል። አንድ ሶስተኛው የኢሮብ መሬት፣ ባድመ፤ እንዲሁም የኛ ግዛቶች አይደሉም ተብለው በመሞገት የግልግል ዳኞችን እጅ በመጠምዘዝ ያስረከቡት ፆሮናና ፎረት ካዶርኖ፣ ...... ወዘተ ለሻዓቢያ ተሰጥቷል። አቶ መለስና የሚመሩቱ ኢህአዴግም "የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ድላችን እውን ሆነ።" ብለው ዘግቷል። ለኢትዮጵያ ቀናኢ የሆነ መንግሥት፣ የሚዋጋው ላንድ ትርጉም አልባ ግዑዝ ሕግ የሚባል መጠርያ ላለው ነገር አይደለም። ጦርነት የሚያካሂደው ለሉዓላዊ ህዝብና መሬት መከበርና መታፈር ነው። በመሆኑም ጦርነት የሚካሄድበት ቦታ በሕግ የራስህ ቦታ መሆን አለበት። በመሆኑም ኢትዮጵያ የተዋጋችው የራሷን ግዛት የማስጠበቅ ሕጋዊ ጦርነት እንጂ ቦታው ላልተወሰነ ሕግ ማስከበር እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት። ውጤቱም በማያሻማ ልዩና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እስከዘለቄታው ያስረገጠና ያስከበረ መሆን ነበረበት። አገራችንም የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የሚፈቅድላትን ራስን የመከላከል ሙሉ መብት ተጠቃሚ መሆን በተገባት ነበር። ስለዚህ እነዚህ የ"ሉዓላዊነታችን ተከብሯል" ሰባኪ ብልጣብልጥ ተላላኪዎች፤ በአቶ መለስና በሚመሩት ፓርቲ ግልጽ ተደርጎ የተነገረውንና ፀሐይ የሞቀውን እውነት በማድበስበስ "መንግሥታችን ሉዓላዊነታችንን አያስደፍርም" እያሉ ህዝብን

ከማደናገር  ቢቆጠቡ ይሻላል። ለመብላት ሲባል መበላትም እንዳለ ማወቅ ብልህነት ነው! ብልጥ ከመሆንም ብልህ መሆን ይመረጣል!!!

ኢህአዴግም አገሮች ጦርነት የሚካሄዱት ወደው ሳይሆን ሉዓላዊነታቸውንና ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር እንደሆነ ቢረዳው ይበጃል። ሉዓላዊ ግዛትህን ለመከላከል የግድ ወርቅና አልማዝ እንዲኖርበት አያስፈልግም። ባድመ ወርቅ ይኑራት አይኑራት፣ የኢሮብ መሬት ወርቅ ይኑረው አልማዝ በመጀመርያ ደረጃ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች በመሆናቸው ብቻ ሊከበሩና ሊጠበቁ ይገባል። ስለ ወርቅም ሆነ ኣልማዝ መኖር አለመኖር ጥያቄ የሚነሳው ከዛ በኋላ መሆን አለበት። ወርቅ ወይም አልማዝ ስላለበት የሌሎች አገሮችን ግዛት መውረር አንችልም፣ መውረርም የለብንም። ወርቅ ኖረው አልኖረው የራሳችን የሆነውን ሉዓላዊ ግዛትና ህዝብንም ማስወረር የለብንም። ለነገሩ እነዛ ግዛቶች ውስጥ ለተወለድን ወገኖች እነዛ ቦታዎች ከወርቅም ከአልማዝም ሆነ ከሌላ አለ ከሚባል ማዕድን እንደሚበልጡብን ይገባቸው ይሆን?

**ማጠቃለያ**

በመጀመርያ ደረጃ የአንድ አገር  መንግሥት ከማንም በላይና በፊት ለሚያስተዳድረው ህዝብ በቃልም በተግባርም ታማኝ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል። የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከት ይህ ታማኝነት የሚባል ጉዳይ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርብን ሆነናል። ተቆርሶ ስለተሰጠው ዳር ድንበራችንና የአቶ ሥዩም መስፈን "በሕግ ፊትም አሸንፈናል" አሳፋሪ ንግግር የሚያዝናናን ሆኖ አልተገኘም፤ ዋሽቴውናል። ይህ አባባላቸው ህዝብን ለማሞኘት የተደረገ አጉል ሙከራ ከመሆኑም በላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ተክለ-ሰውነት ጭምር የጎዳ ሆኖ ለታሪክ ተመዝግቧል። በዚህ የኤሌክትሮኒክስ ዘመን ያልሆነውን ይዞ መቅረብ ረጅም መንገድ የሚያስኬድ ሆኖ አልተገኘም። ከመቅጽበት የመጋለጥ አደጋን ያስከትላል። የአቶ ሥዩም የአሸንፈናል መግለጫም የገጠመው ችግር ይኸው ነው። እሳቸው መግለጫውን በሰጡበት ቅጽበት ነበር የሄጉ ውሳኔ በድረ-ገፆች ላይ የተሰራጨው። የአከባቢው ተወላጆችና አከባቢውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ኢትዮጵያዊያን ባያጋልጡት ኖሮ በጦርነቱ ወቅት በስም ያልተጠቀሱና የሄግ ውሳኔ ለኤርትራ የከለላቸው ግዛቶቻችን በኢትዮጵያ ህዝብ ሳይታወቁ የማለፍ ዕድል ሊገጥማቸው ይችል እንደነበረ ግልጽ ነው። ሕወሓት/ኢህአዴግ ከኢሮብ ለኤርትራ ስለተሰጡት ግዛቶች አንድም ቀን በይፋ ለመናገር የማይደፍረውም በዚህ ምክንያት ነው። አቅም ይወስነን እንደሆነ እንጂ ልንታለል ፈጽሞ አንችልም። መሬታችንን አስመልክቶ ሳር ቅጠሏን እናውቃታለን። በመሆኑም ነው ለዘላቂ ሰላም ዳር ድንበሩን የማካለል ተግባር ውስጥ ታማኝ የአገር ሽማግሌዎች ያለ አንዳች ተፅእኖ በነፃነት ይሳተፉ የሚል ጥሪ የሚስተጋባው። እንኳን ሄግ የተቀመጠው የፈረንጅ ዳኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥትም ከኛ በላይ ስለ ዳር ድንበራችን ሊነግረን አይችልም፤ አይገባምም። እውነት ትንገስ፤ ማታለል ይወገድ ይቀበር።

አቶ መለስም ሆኑ በርሳቸው የሚመራው ኢህአዴግ ለኢትዮጵያና ለዜጎቹዋ ታማኝ መሆናቸው ቢገልጹም፤ በቃላት ካልሆነ በተግባር የሚታየው ሃቅ የሚያሳየን በተቃራኒው ያለውን ነው። በጎ ቃላት ለብቻቸው ተአማኒነትን አይፈጥሩም። የኢትዮጵያ ህዝብ በአገዛዙ ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደረገውም የሚነገረውና በተግባር የሚታየው ለየቅል በመሆናቸው ነው። አቶ መለስና የሚመሩት ኢህአዴግ ለሉዓላዊነታችን መከበር ካላቸው ተአማኒነት ይልቅ ለአበዳሪዎች ያላቸው ከበሬታ ይበልጥባቸዋል። ይህንን በሚመለከት ከላይ በዝርዝር ለማቅረብ የተሞከረው እንዳለ ሆኖ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት መገባደጃ ላይ በቀረበው "ቴክኒካል አሬንጅመንት" ሰነድ ላይ ውይይት ሲካሄድ የነበረውን የአቶ መለስ አቋም እንፈትሽ።  በዛ መልከ ጥፉና ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን አሳልፎ በሰጠ ሰነድ ላይ የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ሲመክር አቶ መለስ የያዙት አቋም አቶ ስዬ ከላ በተጠቀሰው መፅሐፋቸው ውስጥ ገጽ 56 ላይ እንደሚከተለው አስፍረውት ይገኛል።

> "…………መጨረሻ ላይ "ቴክኒካል አሬንጅመንት" የሚባለውን ሰነድ ከአልጀርስ አመጣና ይህንን እንቀበል ካልተቀበልን ግን "አሜሪካውያን እንኳን ለወዳጅ ለጠላትም የማንመኝለት ቅጣት እናውርድባችኋለን የሚል ማስጠንቀቅያ ሰጥተውናል" ከሚል ማስፈራሪያ ጋር ጋሻ ጃግሬዎቹ የሆኑትን አቶ ስዩም መስፍንና አቶ ብርሃነ ገብረክርስቶስን አስከትሎ መጣና ሰጠን።"

እዚህ ላይ አቶ መለስ ለአሜሪካኖች ኩርፊያ ምን ያህል እንደሚጨነቁና የውጭ ኃያላን ገቶቻቸውን ምን ያህልእንደሚፈሩ በግልጽ ለማየት ይቻላል። አቶ መለስ ከአሜሪካኖች ማስፈራርያ ለማምለጥ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመሰዋት ከመጀመሪያውም ዝግጁ እንደነበሩና በግልጽ ይታያል። ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን አሳልፈው ከመስጠት ወደ ኋላ የማይሉ መሆናቸውም ያሳያል። ውጭውጩን የሚነገረን ሉዓላዊነትን አናስደፍርም የሚለው የተለመደ ዘፈን "የድመት ማንቀላፋት አይጥን ለማታለል" የሚለው ተረት እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

መጨረሻ ላይ የህወሓት ካድሬዎች የኢሮብ ህዝብን እየሰበሰቡ እኛ ተከራከርን! ምን እናድርግ አሁን ሄግ ወስኖብናልና የተወሰነለትን መሬት ለሻዓቢያ ማስረከብ አለብን ብለው ሲያስፈራሩና ሲሰብኩ መከረማቸው ለዋዛ አልነበረም። ህዝቡ ግን የሚበገር አልሆነም። የምትለግሱት መሬት ካላቹህ ያኔ እናያለን እያለ ነበር መልሶ የዘተባቸው። የመሬት ማካለሉ ጉዳይ እስካሁን የተራዘመውም በዚህ ምክንያት እንጂ በገዢዎቻችን ብርታት አይደለም። "አንድ ቤት ለሁለት እንዳይከፈል፣.....ወዘተ " የተባለለት የአቶ መለስ ባለ 5 ነጥብ የማካለያ ሓሳብ የቀረበውም የህዝቡ እምቢታ ጠንክሮ ከቀጠለ በኋላ ለሥልጣን አደጋ እንዳይሆን ጊዜ መግዣ ነው። ባይሆን ኖሮ እነ አቶ መለስ አንድ ቀን አምልጧቸው እንኳ የነዛ 100 በላይ ታጋች የኢሮብ ተወላጆች ስም አንስተው ዜጎች ተወስደውብን ድኳቸው ጠፍቷልና ሻዓቢያ ዜጎቻችንን ይመልስ ለማለት ድፍረቱ ይኖራቸው ነበር፤ አልሆነም። አቶ መለስ ዓላማቸው የሻዓቢያን ሠራዊት መደምሰስ ይሁን የሚለውን ሃሳብ ለመቀበል እቸገራለሁ" (የአቶ ስዬ መጽሃፍ ገጽ 17 ይመልከቱ) ያሉትም ያለ ምክንያት አልነበረም። አገራችንን ወሮ ዜጎቻችንን እየጨፈጨፈ የነበረ ሠራዊት መደምሰስ የሚለውን ዓላማ አለመቀበል ማለት፣ ሉዓላዊነትን የማስከበር ጦርነት ማካሄድ የለብንም ከማለት ውጭ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም። ስለሆነም ኢህአዴግ ዛሬም ቢሆን ሉዓላዊነታችንን አሳልፎ ከመስጠት የሚመለስ ኃይል አይደለም። የሚጠብቀው ምቹ ጊዜ እስኪገኝ ብቻ ነው። ያ ምቹ ጊዜም በመድረስ ላይ ያለ ይመስላል።

ዛሬ ኢህአዴግ ውስጥ አሻፈረኝ ለማለት የሚችል ሰው ካለ በሂደት የምናየው ይሆናል። ያች አቶ መለስ የሚፈሯት የአሜሪካኖች ማስፈራርያ አሁንም መንገድ ላይ ያለች ትመስላለች። የአሜሪካ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ኢትዮጵያን በሚመለከት አንድ ሰነድ (Bill) ነድፎ ሕግ ሆኖ እንዲወጣ በመወያየት ላይ ነው። ይህ S.3757 ተብሎ የሚታወቀው የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ሊከተለው የሚገባ  አቋምን የሚያመላክት ሰነድ ነድፎ ለሕግ መወሰኛው ምክር ቤት የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ መርቶት ሕግ ሆኖ እንዲወጣ እየተጠበቀ ነው። ይህ ሕግ ከላይ በተመለከተው መልክ ሉዓላዊ ግዛቶቻችንን አሳልፎ ለመስጠት ለአቶ መለስ ምክንያት ሊሆናቸው የሚችል አንቀጽ በሚከተለው መልክ ተካትቶ ይገኛል። ክፍል 4 ፓራገራፍ 5 ላይ፤

> "ሁለቱም የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት በመካከላቸው ያለውን ውጥረት ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎችን ባስቸኳይ እንዲወስዱ፤ የኢትዮጵያ-ኤርትራ የድንበር ኮሚሽን በሰጠው ብይን መሠረት አካላዊ የድንበር ማካለሉን እንዲተገብሩና በሁለቱ አገሮች መካከል ጤነኛ ግንኙነት እንዲፈጠር ማበረታታት" (ግርድፍ ትርጉም በፀሐፊ) ይላል። ከዚህ በታች በእንግሊዝኛው እንዳለ ሰፍሯል።
>
> (5) encourage the Governments of both Ethiopia and Eritrea to immediately take steps to lessen tensions, physically demarcate the border in accord with the Ethiopia-Eritrea Border Commission decision, and promote normalization of relations between  the two countries.

እንግዲህ ይህንን ከላይ "ቴክኒካል አሬንጅመንት"ን ካልተቀበልን አሜሪካኖች እንኳን ለወዳጅ ለጥላትም የማንመኝለት ቅጣት እናወርድባችኋለን" ብለውናል በማለት ያቀረቡትን ሙግት ልብ ብለን ካየነው፤ ይኸው ዛሬ ለብቻቸው ኮርማ የሆኑበት ኢህአዴግ ምን እንደሚያደርግ ለመገመት የሚከብድ አይደለም። ማበረታታት "encourage" የሚለው ቃል እንዲሁ የዲፕሎማሲ ቃል እንዳይሆን መስጋቱ ብልህነት ነው። በዲፕሎማሲው ዓለም "እናስገድዳለን" ብሎ መናገር አጸያፊ በመሆኑ ካልሆነ፤ አሜሪካኖች አቶ መለስ ምን ያህል ሊለሳለሱ እንደሚችሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ስለሆነም የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ያወጣው ረቂቅ ሕግ ሆኖ ከፀደቀ አቶ መለስ ላይ የሄጉን ብይን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጫና መፍጠራቸው የማይቀር ነው። አቶ መለስ ደግሞ እንደ አመሜሪካ ያለ ዞርያ ምላሽ እርዳታ የሚሰጣቸው ኃይል የሚፈጥርባቸው ጫናን የመቋቋም አቅምና ፍላጎት አይኖራቸውም። ይህ ሃቅ በ"ቴክኒካል አሬንጅመንት" ሰነድ ላይ ክርክር ሲያደርጉ ገሃድ ሆኖ ወጥቷል። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ አቶ መለስ የአሜሪካኖችን ሁለመናዊ ድጋፍ ከምን ጊዜም በላይ የሚፈልጉት ነው። ለወደፊቱ አማራጭ ይሆናሉ የሚባሉት ቻይናዎች በአሁኑ ሰዓት አሜሪካኖችን ወይም በጅምላ የምእራቡን ዓለም ተክተው ሁለመናዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል አቅም ገና አልገነቡም። በዛም ተባለ በዚህ አቶ መለስ ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለሻዓቢያ ለማስረከብ እንደ ምክንያት ሊያቀርቧቸው የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸው ያሉ ይመስላል። ዛሬ አሜሪካኖች "እንኳን ለወዳጅ ለጠላትም የማንመኝለት መዓት እናወርድባቹሃለን" ብለውናል ቢባል ወግድ የሚል የካቢኔ አባል የለም።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ህዝብ ብርቱ ጫና ካልታከለበት እስካሁን ሳይካለል በእንጥልጥል የቆየውን ሉዓላዊ ግዛታችን በሌላ ሽወዳ ለሻዓቢያ የማስረከብ አጀንዳ እንደገና ሊከሰት ይችላል ብሎ መጠርጠር ተገቢ ነው። ይህ "መንግሥታችን ቃል ገብቶልናል፤ ዳር ድንበራችን አይነካም" የሚለው የብልጣብልጦች አሉባልታ ለደቂቃም ያህል ሊያዘናጋን አይገባም። እላይ እንደተገለጸው በነአቶ መለስ የሚነገሩ ለጆሮ "የሚጣፍጡ" ዓረፍተ-ነገሮች በአየር ላይ ተነው ሲጠፉ በተግባር ተመልክተናል። የሚነገረንና ተግባር ላይ የሚውለው ለየቅል መሆኑን ካስተዋልን ውለን አድረናል። የነአቶ መለስና ጋሻ ጃግሮዎቻቸው ቃላቶች የማሳመን አቅማቸው ወድቋል። ከዚህ በፊት ያስተዋልናቸው ነገሮች እነሱ በሚሉን ላይ እምነት

እንዳይኖረን አድርገውናል። ባጭሩ መተማመን ጠፍቷል። እነሱ ጋር ያለን ያለፈው ልምድ ለዛሬና ነገ ትምህርት ቤት ሊሆኑን ይገባል። የምናዳምጣቸው የትላንቱን በልቦናችን በመያዝ ከዛሬው ጋር በማገናዘብ እንጂ፤ የትላንቱን እየረሳን መሆን የለበትም። ካልሆነ ግን ጆርጅ ሳንታያና "Those who cannot remember the past are condemned to repeat it". "ያለፈውን ማስታወስ የማይችሉ ሊደግሙት የተፈረደባቸው ናቸው" ይለናልና፤ እርግማኑ እንዳይደርሰን እንጠንቀቅ።

የኢህአዴግ መሪዎች በምርጫ 2002 ዓ.ም በማጭበርበር የተገኘውን 99.6% ድምፅ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ኢህአዴግ ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸው ድንቅ የልማት ክንዋኔዎችን በማድነቅ በውጤቱ ረክቶ ነው ይህንን ድምጽ የሰጠን በማለት በየመድረኩ እያፌዙ ናቸው። ያለፉት ዓመታት ክንዋኔዎቻቸው የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ውዝግብና ውጤቱን እንደሚያጠቃልል ወይም ዘንግተውታል አለያም የኢትዮጵያ ህዝብ ውጤቱን በጸጋ ተቀብሎታል የሚል አጉል ራስን የማወደስና በውድቀት መኩራራትን ያመላክታል። ከዛም አልፎ ለወደፊት ዳር ድንበራችንን አሳልፎ በመስጠት ሽንፈታቸውን በህዝብ ለማላከክ ዳር ዳር እያሉን ሊሆን ይችላል። መጨረሻውም የሄጉን ውሳኔ ተግባራዊ አድርገው ህዝቡ እኮ የመረጠን ይህንን ተግባራችንን አወድሶ ዳር እንድናደርስለት ነው! የሚል የጅላጅል ቀልድ ይዘውልን ብቅ እንዳይሉ ያሰጋል። ስለሆነም፤ ዳር ድንበራችንን የማስከበር ሓላፊነት በኛ በዜጎች ጫንቃ ላይ የተጣለ መሆኑን መዘንጋት የለበትም። ያለፈውን እናስታውስ!!!!!

አንድ መዘንጋት የሌለበት ሃቅ ቢኖር፤ ዳር ድንበሩን አሁን ባለበት መልኩ ህዝብን ሳያሳትፍ ማካለል ማለት የአከባቢውን ሰላም እስከወዲያኛው ደህና ሁን ብሎ እንደመሰናበት የሚቆጠር ነው።

ከዚህ በተረፈ ከገዥዎቻችንም ሆነ ከሻዓቢ በኩል አድማጭ ይኖራል የሚል ቅንጣት ታክል ተስፋ ባይኖረውም፤ ይህ ፀሐፊ የሚከተሉትን መልእክቶች ሳያስተላልፍ መደምደም አይሻም።

1. በ1990 ዓ.ም ሻዓቢያ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛቶች በወረራ ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ አግቶ የወሰዳቸው ከ100 በላይ የኢሮብ ተወላጆችና ሌሎች ከድንበር አከባቢ የተጠለፉ ኢትዮጵያዊያንን የኢህአዴግ መሪዎች ሓላፊነት ወስደው ዜጎቻችንን ወደ አድራሻቸው እንዲመልስ ሻዓቢያን እንዲጠይቁ፤ ዜጎቻችን እስኪመለሱ ድረስም አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ ኢትዮጵያዊያን በኢህአዴግ ላይ ጫና እንዲያሳርፉ፤
2. "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ይባላልና ሻዓቢያ የሚደረግለትን ጥሪ የማይቀበል መሆኑ የታወቀ ቢሆንም ኤርትራዊያን ወገኖች እነዚህ ሰዎች እንዲፈቱ ጥሪ እንዲያቀርቡና ለማስፈታትም የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ፤
3. የዳር ድንበራችን ጉዳይን አስመልክቶ፤ እያደረና ጊዜ እየፈጀ በሄደ ቁጥር የሁኔታዎች መለዋወጥ ቢከተል ይራቅ ይቅረብ መንግስታቱህ የፈረመው ውል ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚል ጫና ሊፈጥር ስለሚችል፤ ከመጀመርያውም መፈረም ያልነበረበት ውል ነውና የአልጀርሱን ውል የኢህአዴግ መንግሥት ራሱ ሻዓቢያ ያፈረሰውን ትርጉም አልባ ውል ታቅፎ መቀመጡ የሚያስከትለውን ጣጣ ግምት ውስጥ በማስገባት የፈረመውን ውል ውድቅ እንዲያደርግ ህዝባችን ጫና እንዲያደርግበት፤
4. ኤርትራ ጋር ያለን የድንበር ውዝግብ ምን ላይ እንዳለ አይተኗል። አሁን ደግሞ ከሱዳን መንግሥት ጋር የድንበር ማካለል ድርድር በጓዳ እየተካሄደ መሆኑ እየተሰማ ነው። ከኤርትራ ጋር ከርክር እንበለው ምክክር ያሸከመንን ዓይነት ሽንፈት መደገም የለበትም። በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ የመደራደርያ ጭብጦችን የማወቅ መብት አለው። ስለሆነም፤ ኢህአዴግ የመደራደርያ ጭብጦችን ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ እንዲያደርግ የኢትዮጵያ ህዝብ ጫና እንዲያደርግበት ጥሪውን ያስተላልፋል።

ሉዓላዊነታችን ክብራችን ነው!!!!!

ጥቅምት 2003